## የታሪክ ተጠያቂወች መሆናችንን ለማቆም እንችላለን፤

## ኢትዮጵያ ከመለስ ባሻገር፤ የማይገኝ እድል ወይንስ የባሰ ፈተና?

ክፍል አስራ አንድ

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

*መግቢያ፤*

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከታታይ ችግር፤ የስልጣኑ ባለቤት አለመሆኑ ነው።** ይህ ሕዝብ፤ ለሙብቱ ስኬታማነት፤ ለሃገሩ ክብርና ግዛታዊ አንድነት ያደረገው ትግል፤ የከፈለው ዋጋ፤ ሁላችንም የሚያኮራ ነው። ለስኬታማነቱ ማነቆ የሆነው ሕዝቡ ሳይሆን፤ ለሕዝቡ ቁመናል የምንለው ድሃው ህብረተሰብ ያስተማረን እኛው የፖለቲካ ተወናዋዮች ነን። ድክመታችንና ጥንካሪያችን ረጋ ብለን መመርመርም ያለብን እኛው ነን። ያፖለቲካ ባህል ለውጥ የሚያስፈልገን መሆኑን፤ በሃቅ፤ በጥበብ መመርመርና **ብሩህ አማራጭና አቅጣጫ ማቀርብ ያለብን እኛው ነን።** ወቅቱ ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። በእኛ እድሜ፤ ሶስት የመንግስት ለውጦች አይተናል፤ የአጼ ሃይለስላሴ ንጉሳዊ፤ ፊውዳላዊ፤ የመንስቱ ሃይለማሪም ወታደራዊ አምባገነን ሶሻሊዝም፤ የመለስ ዜናዊ፤ የጠባብ ብሄርተኛ የአንድ ፓርቲ የበላይነት። አንጻራቸው ይለያይ እንጅ፤ እነዚህ መንግስታት፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማህበረሰብ፤ የስራ እድል፤ የትምህርት፤ የሃይማኖት አድሎና የጥቅም የበላይነት አሳይተዋል። የሃይሉ ሚዛን፤ የጥቅሙ ክብደት ተመሳሳይ ባይሆንም፤ ተከታታይ መንግስታት፤ በሃገራችንና በተራው ህዝብ ላይ ያስከተሉት በደል ክብደት ያለው ነው ለማለት ይቻላል። ማለትም፤ የተራውን ህብረተሰብ ችግር ሊፈቱት አልቻሉም። የገዡውን ክፍል ያገለግሉ ስለነበር፤ የልዩ፤ ልዩ፤ ህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር በጥበብና በዘላቂነት ሊያስወግዱት አልቻሉም። ከህዝብ ድምጽና ስልጣን አንጻር ሲታይ፤ ተከታታይ መንግስታት ጥለውልን ያለፉት ችግር እንጅ መፍትሄ አይደለም። ሆኖም፤ እነዚህ ተከታታይ መንግስታት ልዩነቶችም ነበሯቸው። የአጼ ሃይለ ስላሴ መንግስት ከሁለቱም ይለያል። አሁን፤ ይህ አዙሪኝ የሆነ (**Vicious Cycle**) የፖለቲካ ባህል እንዲለወጥ ትንሽ ቀዳዳ ተከፍቷል። ዋናው ጥያቄ፤ ይህን እድል ለመጠቀም ምን ያህል ተዘጋጅተናል፤ ምን ያህል ፈቃደኛ ነን፤ ምን ያህል ጥበበኛ ነን? የሚለው ነው። በእኔ እምነት፤ የአሁኑ እድል ካመለጠን፤ ማንንም ለመውቀስ አንችልም፤ መውቀስ ያለብን እኛኑ ነው።

አንድ የምንጋራው አበይት ጉዳይ ቢኖር፤ የህወሓት/ኢህአዴግን መንግስት ከሁለቱ የሚለየው ዋና ራእይ፤ **የመለስ አመራር** "በማይታረቅ፤ የብሄር ልዩነት" የታነጸ መሆኑ ነው። እኔ፤ "ብሄሮች የማይታረቅ ልዩነት አላቸው" የሚለውን መሰረተ ሃሳብ አልቀበልም። ይህን የህወሓት አመራር የሚለውን ልዩነት ጥበብ በተሞላ፤ በጦር ሃይል በተረዳ መንገድ ተጠቅሞበታል። መለስ፤ አምባገነንነትን እንደ ተፍጥሮ ህግ፤ እንደ ሕዝባዊ አገልግሎት አድርገው አለምን ያሳመኑበትን ምክንያት እዚህ አልተችም። መጥቀስ የምፈልገው፤ የማይታረቅ የብሄር ልዩነት፤ የአምባገነን ስርአት አደጋው ከፍ ያለ መሆኑን ነው። በመለስ ዜናዊ የተመራው መንግስት የታላላቅ፤ በተለይ፤ የምእራባዊያንን፤ በቅርቡ ደግሞ፤ የቻይናን አመኔታና ድጋፍ በማግኘቱ፤ አገራችን ያልታየ እድገት (Growth) አስመዝግባለች እየተባለ ይነገራል። በሃይል ማመንጫ ግድብ፤ በመንገድ ስራ፣ በትምህርት ስርጭት፤ በጤና ጣቢያወች ስፋት፤ በህንጻ፤ በከተሞች ስፋት፤ ወዘተ ያሳየው ለውጥ ሊናቅ አይችልም፤ የሚታይ ነው። ሆኖም፤ እድገቱ አያስደንቅም። የማያስደንቅበት ዋና ምክንያት፤ ከሁለቱ መንግስታት ጋር ሲንጻጸር፤ መለስ የመሩት መንግስት ከልዩ ልዩ ለጋስ መንግስታት፤ ድርጅቶችና የግል ተቋሞች ቢያንስ **US$40 billion አግኝቷል።** በስደት ላይ የሚገኘው አሁን ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚገመተው ስደተኛ፤ የእድገቱ ተካፋይ ሁኗል። ቢያንስ፤ በአመት ሶስት ቢሊየን፤ ሰባት መቶ ሚሊዮን ዶላር ይልካል። ተሳትፎው ጎልቶ የሚታየው በተለይ

በፍጆት ስራ፤ በቤት ባለቤትነት፤ በግል ህንጻ፤ በምግብ ተቋሞች፤ በሆቴሎች፤ ወዘተ፤ በቤተሰብ፤ ዘመድና ጓደኛ በመደጎም መስከ ላይ ነው። ይህ በፍጆት ላይ የተመሰረተ እድገት፤ መዋቅራዊ ለውጥ አላመጣም፤ ኢትዮጵያ የባሰውን ጥገኛ ሁናለች። ሕዝቡ፤ በተፈጥሮ ሃብቱ ለማዘዝ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በሃገሩ ድምጽ፤ መብት የለውም።

አለም ባንክ እንደሚገምተው፤ ቢያንስ አምስት ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን የሚደገፉት ስደተኛው በሚልከው ገንዘብ ነው። ሌሎች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አሁንም፤ የእለት ምግብ የሚያገኙት ለጋስ የሆኑ መንግስታትና ድርጅቶች በሚሰጡት ገንዘብ/ርዳታ ነው። ከሁለቱ መንግስታት ጋር ሲወዳደር፤ የሃይለ ስላሴ መንግስት የእርዳታ ማስረጃ **መሰብሰብ** (**Aid flow data**) ከጀመረበት አንስቶ ያገኘው **US$150 million**፤ ይገመታል። ሳይሰረቅ ከስራ ላይ ዉሏል። የወታደራዊ መንግስት፤ በተለይ ከሶቬት ህብረት ለመሳሪያ መግዣ ያገኘውን ጨምሮ፤ **ከ1974-1991 US$3.4 billion ብቻ በርዳታ አግኝቷል።** የህወሓት/ኢህአዴ አንድ አስረኛ መሆኑ ነው። አብዛኛው ለመሳሪያ፤ አገር ለመከላከል የዋለ። ደርግ፤ ከአሜርካ፤ ከእንግሊዝ፤ ከአለም ባንክ ርዳታ አያገኝም ነበር። ከህወሓት/ኢህአዴግ በፊት የነበሩት፤ ሁለቱ የኢትዮጵያ መንግስታት ከእርዳታ የተገኘ ገንዘብ በማሸሺ (**Massive Illicit Transfer**) አልተከሰሱም። ለመስረቅ፤ ብዙም መፈናፈኛ አልነበራቸውም።

በአንጻሩ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በሙስና፤ በአድሎና ፤ከህግ ውጭ ገንዘብ በማሸሺ በሃገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል። በአመት፣ <u>**ቢያንስ፤ US$ 3 billion ከህግ ውጭ ከሃገር ይወጣል፤**</u> ይሰረቃል። ሙስናና ከህግ ውጭ የገንዘብ ሽሽት ባይኖር፤ ስርአቱ ተሳትፏዊና ፍትሃዊ ቢሆን፤ የኢትዮጵያ የእድገት ደረጃ ከፍ ባለ ነበር። ቢያንስ፤ ሕዝቡ፤ አስተማማኝ የምግብ ዋስትና ያገኝ ነበር። የስራ እድል በብዛት ይከፈት ነበር። የዋጋ ግሽፈት ሊገታ ይችል ነበር፤ ወዘተ። የተገኘው እድገት ዘላቂነትና ፍትሃዊ ሊሆን አልቻለም የምለው ለዚህ ነው። ፖሊሲው ለፍትህ የታሰበ አይደለም። የነፍስ ወከፍ ገቢ ፍጹም ድሃ ከተባሉት እንደ ናይጀር፤ እንደ ዝምባብዌ ካሉት ሊለይ አይችልም። የአፍሪካ አማካኝ የነፍስ ወከፍ <u>**ገቢ US$1,070 ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አሁንም US$365 (በአመት) ነው።**</u>

"አስደናቂ እድገት ተጎናጽፋለች" በምትባለው ኢትዮጵያ የገቢ ልዩነት እየሰፋ መሄዱ፤ በድሃና በሃብታም መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱ፤ ሊገታ የማይችል የዋጋ ግሽፈት የሰውን ኑሮ መጉዳቱ፤ የወጣቱ እድል ተምሮ መሰደድ ተደጋጋሚ መሆኑ፤ ወዘተ፤ ፖሊሲውና መዋቅሩ የፈጠራቸው፤ ያለለውጥ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ብቻውን ሊፈታቸው የማይችል መሆኑን የሚያሳዩ መለኪያወች ናቸው። ነጻነት፤ የህዝብ ድምጽና ቀጥተኛ ተሳትፎ አለመኖሩ፤ ስርአቱ ለፍትህ፤ ለሰላም፤ ለእርጋታ፤ አብሮና ተቻችሎ ለመኖር፤ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ለማጥፋት፤ "ሽብርተኝነትን" ለማስወገድ፤ አስጊ ሁኔታወችን ፈጣሪ እንጅ፤ መፍትሄ ሰጭ አለመሆኑን የሚያሳዩ መለኪያወች ናቸው። ስርአቱ፤ እነዚህን ችግሮች አባባስ እንጅ ቀነሰ ለማለት አይቻልም፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ሃገራችን ከኋላ ቀርነት፤ ከርሃብ፤ ከስደት፤ ከጥገኝነት፤ ከተስፋ መቁረጥ ነጻ ለማድረግ አልቻለም።

ገዢው ፓርቲ የእነዚህን ችግሮች መኖር ለመካድ አይችልም። ሌላ ቀርቶ፤ አድናቂ የሆኑ መንግስታትና አበዳሪ ድርጅቶች ያውቁታል፤ ያምኑበታል። ጠለቅ ብሎ ያየ ታዛቢ፤ አገር ወዳድ፤ የገዥው ፓርቲ ተራ አባል፤ የጦር ሃይሎች አባል፤ የውጭ ተመልካች፤ ህወሓት/ ኢህአዴግ እነዚህንና ሌሎችን አገራዊ ችግሮች ብቻውን ሊፈታቸው እንደማይችል ይገነዘባል። የአመለካከት ለውጥ አስፈላጊ የሚሆነው፤ አብሮ ተባብሮ ችግሮችን በጋራ መፍታት የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ሁሉን አቀፍ የሆነ የመንግስት ስርአት መፈጠር ያለበት ለዚህ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያስፈልገው፤ "በጠላትነት እየተያዩ፤ ሆድና ጀርባ ሁኖ" መኖርን ነው፤ በጠላትንትና በጥላቻ ባህል የጋራ ችግሮችን ለመፍታት አይቻልም። የሌሎች አገሮች ምሳሌ እንደሚያሳየው፤ ፍትሃዊ፤ ሁሉን አቀፍ፤ ለሁሉም አገልጋይ በሆነ የመንግስት ስርአትና

አመራር ፓርቲወች **በጠላትነት አይተያዩም፤** ጠላትነት የሚመነጨው ዲሞክራሳዊ ስርአትን ከመፍራት ነው። አድሏዊ መንግስት ጠላትነትን ባህል የሚያደርገው ላለመረጋጋት(Permanent Instability and Suspence) ስለሚረዳው ነው።

**አዲስ የለውጥ ምእራፍ፤ አዲስ አቅጣጫ፤**

የዚህ አቅርቦት ዋና አላማ፤ የሃገራችን ሁለ ዘርፍ የሆኑ ችግሮች በጋራ ሊፈቱ ይችላሉ የሚል ነው። አገራዊ ችግሮችን በጋራ ለማስወገድ ከተፈለገ፤ የአንድ ፓርቲ የበላይነት አገዛዝ በአስቸኳ መለወጥ አለበት። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት መሆን አለበት። መንግስትና መሪወች የሕዝብ ተገዥ፤ የሕዝብ አገልጋይ፤ የህዝብ ድምጽ አዳማጭ መሆን አለባቸው። አዲስ የለውጥ ምእራፍ ማለት እንደዚህ ነው። ለእውነተኛ የዲሞክራሳዊ መንግስት መቋቋም እውቅትና ብልሃት ያለው ሽግግር ማድረግ አሰፈላጊ ነው የሚለውን መሰረተ ሃሳብ ህወሓት/ኢህአዴግና ተቃዋሚ ሃይሎች ከተጋሩ፤ (መጋራት አለባቸው ብየ አምናለሁ)፤ ወደዚህ የሚያደርሱ ቅድመ ሁኔታወችን (**Favorable Conditions**) መፍጠርና ማመቻቸት የሁሉም፤ በተለይ የገዥ ፓርቲ መሪወች ታሪካዊ ሃላፊነት **ነው። ማሰብ ያለባቸው፤** አምባገነናዊ አገዛዝ ከአሁን በኋላ አያዋጣም። በአምባነን ስርአት፤ ሰላም፤ እርጋታ፤ አይኖርም። ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት፤ ለመላው ሕዝቧ ሰላም፣ ለፍትህ፤ ለብልጽግና፤ ለእኩልነት፤ ለነጻነት፤ ለክብር፤ ከርሃብ አለንጋ፤ ከጥገኝነትና ከስደት፤ ነጻ **<u>ለመሆን፤ ቁመናል የሚሉ መንግስታት፤ ተቋሞችና ግለሰቦች ሊረዱን የሚገባቸው ህወሓት/ኢህአዴግና ተቃዋሚ ሃይሎች በሙሉ በአስቸኳይ ሁሉን አቀፍ የሆነ፤ ለሰላም፤ ለእርቅ፤ ለፍትህ፤ ለዲሞክራሳዊ ስርአት ሽግግር፤ አገራዊ ስብሰባ እንዲያደርጉ አስተዋጾ በማድረግ ነው።</u>**

ለዚህ ለተቀደሰ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚመኘው አላማ፤ መንፈሳዊ አባቶች፤ የሃገር ሽማግሌወች፤ የታወቁ ምሁራን፤ ወዘተ ድልድይ ሁነው "ተሰብሰቡ፤ ተነጋገሩ፤ አገራችንና ጉራማይሌ ሕዝቧን አስቀድሙ፤ መወነጃጀልን አትቁሙ፤ "ታሪክ ያላችሁና ጥበበኛ መሆናችሁን ለአለም ህብረተሰብ አስመስክሩ" ሊሉና የመተማመን ቅድመ ሁኔታን ሊያጠናክሩ ይችላሉ። **የድርድር ምርኩዞች፤ አገራዊ አንድነት፤ ሰላም፤ እርቅ፤ ይቅር ባይነት፤ እኩልነት፤ የህግ የበላይነት፤ ነጻ ምርጫ፤ የፖለቲካ ውድድር፤ ዲሞክራሳዊ ስርአት፤ ሰብአዊ መብቶች፤ ሊሆኑ ይችላሉ።**

ይህን ስል፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ጥቅሙን ወደ ጎን ትቶ፤ ለሰላምና፤ ለእርቅ፤ ለድርድርና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ግንባታ በሩን በቀላሉ ይከፍታል የሚል "ቅዠት" ውስጥ አልገባም። በመጀመሪያ፤ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ግለሰቦች፤ ስብስቦች ሁሉ፤ መሰብሰብ፤ መደጋገፍ፤ በአንድ ድምጽ፤ ለአንድ አገራዊ አላማ መቆም አለባቸው። በተለይ፤ አገር ውስጥ ያሉት። ይህን ካደረጉ፤ የአለምን **ህብረተሰብ፤ በተለይ፤ የደጋፊ መንግስታትን አቋም ሊለውጡ ይችላሉ። ገዥውን ፓርቲ፤ ለድርድር ከሚያስገድዱበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ያለው እድል ከፍ ይላል። ሕዝቡ እንዲደፋፈር ያደርጋል፤ ወጣቱ ትውልድ በብዛት ወደዲሞክራሳዊ ግንባታው፤ ወደ ሰላማዊ አመጹ እንዲገባ ያበረታታል።** የፍርሃትን ባህል ይቀንሳል፤ ወዘተ።

የገዥውን ፓርቲ ለማሳፈር/ለማጋለጥ ለሚደረገው ትግል አስተዋጾ ያደርጋል። ያልተሞከረው መሞከር አለበት የምለው ለዚዝ ጭምር ነው። ሆኖም፤ <u>የሰላማዊ አገራዊ ሁሉን አቀፍ ስብሰባና ድርድር ጥሪ፤</u> ቀላል ይሆናል የሚል ግምት የለኝም። ምኞትና ህልም ሁኖ ሊቀር ይችላል፤ መሞከር አለበት የሚል እምነቴ ግን ጠንካራ ነው። ለዚህ ስኬታማነት ቅድመ ሁኔታወችን ተጠቅሞ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት ሊያደርግ የሚገባውን ጥያቄወች ለአለም ሕዝብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለመሰልቸት፤

ማቅረብ፤ ማስረዳት የተቃዋሚወችና የእያንዳዳችን ሁሉ ሃላፊነት **ነው።ከጦርነት ባህል፤ ወደ እርቅና ድርድር ባህል መራመድ ለሃገራችን ዘላቂነት፤ ለመላው ሕዝቧ፤ ፍትሃዊ/ተሳታፊያዊ እድገት ያመራል።**

**ቅድመ ሁኔታ ምን ማለት ነው? ምን ያካትታል?**

"የቅንጅት/የህብረት መንፈስ" አለ ተብሎ የሚነገርለት አባባል አስተማማኝ የሆኑ መስፈፈሪያወች አሁንም አሉ ብሎ ለመናገር አስቸጋሪ ነው። የመንፈሱ መኖር ዋናው መለኪያ፤ ሕዝቡ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ ያለው ጉጉት ብቻ ነው። ቅንጅትና ህብረት የውሃ ሽታ ሁነዋል። ለመንፈሱ የቆሙለት በእስር ቤት የሚሰቃዩ፤ የተበታተኑት፤ በድብቅ የሚሰሩ፤ በውጭ የሚታገሉ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ በነጻነት እንዲሰሩ ከባድ ጫና ቢያደርግም፤ አገር ቤት ሁነው ቀንና ሌሊት የሚታገሉ የሰላማዊ ለውጥ ደጋፊወች፤ ጠበቃወች፤ አሉ። በተለይ ወጣቶች። ቅድመ ሁኔታወች ይመቻቹ ስል፤ መግለጫ የማደርገው ከዚህ በፊት ቅንጅትና ህብረት ያቀረቧቸውን ስምንት አንኳር ጥያቄወች ነው። ጥቅማቸው፤ ተገቢነታቸው አልተለወጠም። እነዚህን በቅደም ተከተል አቀርባለሁ፤

i) የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ይፈቱ። ለነጻነትና ለህይወት ትርጉም ሊሰጥ የሚችልው የመጀመሪያ መለኪያ፤ የታሰሩ ሲፈቱ፤
ii) ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲወች፤ የማህረሰብ ድርጅቶች፤ ግለሰቦች መገናኛ ብዙሃን የመጠቀም መብታቸው ይጠበቅ፤ የፕሬስ ነጻነት ከስራ ላይ ይዋል፤ የፕሬስ ነጻነት ገደብ የሆነው፤ የሽብርተኝነት ህግ ተብሎ ንጹህ ኢትዮጵያዊያን የሚታሰሩበት ህጎች ይወገዱ። የፕሬስ ነጻነት ለዲሞክራሳዊ ስርአት ግንባታ ቁልፍ ነው፤
iii) ህወሓት/ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠረው የምርጫ ቦርድ እንደገና ይዋቀር፤ ከገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያለ አድሎ ያገልግል፤
iv) የጦር ሃይሎች በሙሉ፤ በፖለቲካ ውድድር ውስጥ ጣልቃ መግባታቸውን ያቁሙ፤ ከገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ ሁነው፤ አገራቸውንና መላውን ሕዝብ ያገልግሉ፤
v) የህግ ተቋሞች በሙሉ ከማንም ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ ሁነው፤ ህብረተሰቡን ያገልግሉ፤
vi) ከገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆነ ኮሚሽን ተቋቁሞ ሁሉንም ግድያወች ይመርምር፤
vii) የፓርላማ አስተዳደር/አሰራር ዲሞክራሳዊና ግልጽነት ባለው መንገድ ይስራ፤
viii) ከላይ ያሉትን ሁሉ የሚያስተናግድ/ የሚዳኝ ከገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ነጻ የሆነ ኮሚሽን ይቋቋም የሚሉ ናቸው። እነዚህ ቅድመ ሁኔታወች ከስራ ላይ አልወም። ተቀዳሚ ይሚሆኑት፤ በግለሰቦች ነጻነት፤ በህይወት፤ በመደራጀት፤ ላይ ሸክም የሆኑት ገደቦች በአስቸኳይ እንዲወገዱ ማድረጉ ነው። የመተማመንን፤ የመግባባትን፤ የእርቅን እውን መሆን የሚያሳዩ መለኪያወች ናቸው።

እነዚህን ጥያቄወች ከስራ ላይ ለማዋል እስካሁን ያልተደረገ የፖለቲካ ባህል ለውጥ፤ ሂደትና አቀራረጽ አስፈላጊ ነው። በመጀመሪያ፤ ፈቃደኛነት ማሳየት ያለበት ገዥው ፓርቲ ነው። የኢህአዴግ መንግስት፤ ኢትዮጵያንና መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማእከልና ተቀዳሚ አድርጎ ፤ ለነገዋ ኢትዮጵያ፤ ለሰላም፤ ለሕዝብ ስልጣን የበላይነት፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ለእርቅ፤ ለመግባባት፤ በውይይት ልዩነቶችን ለመዳኘት መሞከር ታሪካዊ ጥሪ እንደሆን ማየት አለበት። እንደዚህ ካየው፤ እንዚህን ቅድመ ሁኔታወች በስራ ይተረጉማል የሚል ግምት አለኝ። ሆኖም፤ ተቃዋሚ ሃይሎች በሙሉ ተባብረው ድምጽ ካላሰሙ፤ ወዶ አያደርገውም የሚሉትን የብዙ ታዛቢወች አስተያየት እጋራለሁ። ሆኖም፤ የሃገራችንና የሕዝቧን ታላቅነት የሚያሳይ ይህ መንገድ መሆኑን መቀበለ ግዴታ መሆኑን ለአለም ሕዝብ ማሳሰብ ግዴታ የሚሆነው ለዚህ ነው። ሰላም፤ እርቅ፤ ይቅር ባይነት፤ ለወደፊቱ ትውልድ ማሰብ፤ የአገርን፤ የህዝብን ችግሮች በጋራ ለማስወገድ መሞከር ያለመድነው ባህል መስሎ ይታያል፡፡ ኢትዮጵያ ለብዙ

ሽህ አመታት ክብሯን፤ ነጻነቷን ይዛ የቆየችው ልዩነቶችን በማቻቻል፤ አብሮ መኖርን በማጠናከር፤ በጋራ ቁሞ፤ የውጭ ጠላትን በመከላከል ነው። ይህን ባህል አድሶ መጠቀም፤ የታላቅነት እንጅ የድክመት ምልክት አይደለም። የዚህ አይነት ለውጥ ለሁሉም ይጠቅማል። ታላቅ የሆነች፤ በፍጥነት የምታድግ ኢትዮጵያን ይፈጥራል፤ መላውን ሕዝቧን ከድህነት፤ ከስደት ነጻ ያወጣል።

አዲሱ "ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚንስትር"፤ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ለዚህ አዲስ ምእራፍ አስተዋጾ እንዲያደርጉ ማበረታታት የሚያስፈልግው ለዚህ ጭምር ነው። በርሳቸው የሚመራው የኢህአዴግ መንግስት ለድርድር ክፍት መሆን የድክመት ምልክት አይደለም፤ ለሃገር፤ ለመላው ሕዝብ የመቆም ምልክት ነው። ለእውነተኛ ዲሞክራሲ፤ ለጭቁን ብሄር/ብሄረሰብ ፍትህ፤ ለነጻነት፤ የመቆም ምልከት ማለት ይህ ነው። በአንጻሩ፤ ለሰላማዊ ድርድር፤ ለእውነተኛ የህዝብ ስልጣን የሚያሽጋግር መንገድ፤ ለፍትህ አለመዘጋጀት የአንድ ፓርቲ አምባገነን አገዛዝ አሁንም ይቀጥል እንደማለት ነው። ይህን አዲሱ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲረዱት፤ ተቃዋሚ ሃይሎች ሁሉ በጋራ፤ ሃየለማሪያም ደሳለኝ፤ ለፍትህ፤ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ እስከቆሙ ድረስ፤ አብሯቸው እነደሚቆም ማሰማት ያለበት አሁን ነው። ከህወሓት የበላይነት ነጻ መኖንን አመልካች ሂደት እርሳቸው የሚመሩት ኢህአዴግ ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ተደራድሮ፤ ለመላው ሕዝብ የሚያገለግል ዲሞክራሳዊ ስርአት መገንባት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የደህንነትና የመከላከያ ሰራዊት የአምባገነን መንግሥት ስርአት ጠባቂና ተከላካይ ሆኖ በ "ጥቁር ቀለም" ታሪክ እንዲፈረጅ መፍቀድ የለበትም። ቃል በገባው የህዝብ **አደራ መሰረት፤ የአንድ ፓርቲ የበላይነት ማገልገል ሳይሆን፤ የወገኑን ብሶት በማየት፤ "የጉራማይሌ** (**Diverse/Mosaic**)" ሕዝቡን አለኝታነትና ክብር፤ የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት ብቻ እንዲያስቀድም፤ መመሪያው እንዲያደርግ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። እውቀት ያላቸው ታዛቢወች እንደሚሉት፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነው የጦር ሃይሉ ተራ አባላትና መካከለኛ እዝ፤ ከመላው ህብረተሰብ የተወጣጣ ነው። ስለሆነም፤ ከአንድ ብሄር የተወጣጣው፤ የትግራይ የበላይ እዝ ሊወክለው አይችልም፤ አይገባም። ስለዚህ፤ አደራውን እንዲወጣ፤ ሃይሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጫና እንዳያደርግ፤ ወገኑን እንዳይገድል፤ መቀስቀስ መወሰን አለበት። እኛም መቀስቀስ አለብን። ለዚህ፤ የቅርብ ምሳሌ አለ።

ውጣ ውረድ ቢያሳይም፤ የግብጽን የጦር ሃይልና የስለላ ድርጅት ከሶሪያው የሚለየው፤ የህዝብ አመጽ ሲነሳ፤ ታንክ፤ የጦር አውሮፕላን፤ መትረየስ፤ የጠበንጃ አፈሙዝ ወደ ሰላማዊው የግብጽ ህዝብ አላዞረም። ባለማዞሩም፤ ከህብረተሰቡ ጎን ቁሟል ለማለት ያስችላል። አገራዊ እንጅ የገዡ ፓርቲ አገልጋይ አለመሆኑን አስመስክሯል። የኢትዮጵያ የጦር ሃይል የሚያኮራ ታሪክ ሊሰራ ይችላል ብየ የምገምተው፤ የራሱ የሚያኮራ ታሪክ ስላለው፤ አገር ወዳድ ስለሆነ፤ አብዛኛው ከህብረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ ስለሆነ፤ ጭምር ነው። ይህ ግምት ብቻ ነው። የሰላም፤ የእርቅ፤ የነጻነት፤ የፍትህ፤ የዲሞክራሳዊ ስርአት ግንባት፤ የመወያየት፤ አብሮ ችግሮችን የመፍታት ጥሪን እንደሚደግፍ ተስፋ የማደርገው፤ አብዛኛ የህብረተሰቡ አንጸባራቂ በመሆኑ ነው። ጠንካራ ኢትዮጵያ ልትኖር የምትችለው ጠንካራና በነጻነት የሚኖር፤ ያለ አድልወ የሚሰራ፤ ሕዝብ ሲኖር ብቻ፤ ነው የሚለውን እሴት ሊቀበል እንደሚችል መገመት አለብን። **<u>ጠንካራ ሕዝብ ያለ ፍትህ፤ ያለ ሙብት፤ ያለ ክብር፤ ያለ ነጻነት፤ ያለ እኩልነት፤ ሊኖር አይችልም ብለን ለመላው አለም ማስረዳት ያለብን እኛው ነን። ይህን የኢትዮጵያ ጦር ሃይል ያውቃል። ጥሪው ሃይሉን የሚመለከተው ለዚህ ጭምር ነው።</u>**

**ከለቅሶው ባሻገር እንይ፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገር አቀፍ በሆነ ሁኔታ፤ ተገዶም ሆነ ፈቅዶ ለመለስ ማልቀሱ፤ በንጹህ ለፍትህ የታገሉ ግለሰቦችን ሞትና መከራ፤ በአብዛኛው ሕዝብ ላይ ያለውን ብሶትና ጭንቀት፤ በወጣቱ ላይ

የደረሰውን አሳፋሪ የስደት እጣ፤ በፍትህ ላይ ያለውን ተደጋጋሚ (**Recurring**) **ጭነት፤** በሃገራችን ላይ የሚታየውንና የሚያንዣበበውን ግልጽ አደጋ ሊበርዘው፤ ልያስወግደው ወይንም ሊሸፍነው አይችልም። ሌላው ሳይቀር ተማሪወች፤ በሆስፒታል የሚታከሙ በሽተኞች በለቅሶው እንዲሳተፉ መገደዳቸው ያሳፍራል እንጅ አያኮራም።

የመለስን እንደማንኛውም ህያው ከዚህ አለም ማለፍ በሰብእነታቸው አስቦ ማዘን/መቀበል የሰው ፍጥሩ ሁሉ ባህርይ ነው። ሆድ የባሰውም ያለቅሳል። እያዘኑ ያለፈውንና የሚመጣውን ማሰብ አስተዋይነት ነው። ከሚያጠያይቁት ነገሮች፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የመለስን "አስከሬን ለምን" ትእይንት አስመሰለው፤ አቀረቡት፤ ሌሎች እንደሚሉት፤ ለምን "አስከሬኑን መነገጃ አስመሰሉት? ለአሁኑና ለተከታታይ ትውልድ ምን መልእክት ለማስተላለፍ ተብሎ ነው? ህወሓት/ኢህአዴግ የቀናት አገር አቀፍ ለቅሶ "ሲያውጅ" የሚያስተላልፈው የአገዛዝ መልክት ስላለው ነውን? ወቅቱ፤ የሰላም፤ የእርቅ፤ የሁሉም ተሳትፎ እውን የሚሆንበት ዋዜማ ነው ለማለት ይሆን? መልእክቱ ምንድን ነው? ለነዚህም ከማውጣት ከማውረድ በላይ መልስ የለኝም። አንዳንዶች እንደሚሉት፤ ስብሰቡ፤ "ትእይንቱ" አያስገርምም ብለን ልናልፍ እንችላለን። ሌሎች ደግሞ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ሰሜን ኮሪያን ሁናለች ብለን እንለፈው። ለመለስ ማለፍ ለምን የዚህን ያህል ለቅሶ አስፈለገ ብለን ስንጠይቅ፤ አምባገነኖች የሚያደርጉትን ማስታወስ ተገቢ ነው። በደርግም ጊዜ ሰው ተገዶ ተሰልፏል። በስታሊን፤ ራሽያም፤ በሰሜን ኮሪያም። ንግግሩ፤ ውይይቱ፤ የውጭ መንግስታት ፕሬዝደንቶችና ተወካዮች ለልቅሶው ለምን መጡ፤ መለስን ለምን አሞገሱ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ፤ ኢትዮጵያዊያን በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጾታ፤ በእድሜ፤ በገቢ፤ በኑሮ ሳይገቱ ለምን አለቀሱ፤ በልቅሶው ወቅት ለምን ሕዝቡ የእምቢተኛነት ስሜት አላሰማም፤ የሚለው አይደለም። ሕዝቡ ለመነሳት የማይችልበት ምክንያት፤ እርህራሄ የሌለው መንግስት ስለሆነ ነው። መግደል፤ ማሰር፤ ማሳደድ ልምዱ ነው። ሌላው እውነት፤ የተቃዋሚ ሃይሉ የፈራረሰ፤ ደካማ፤ የተከፋፈለ ስለሆነ በጀርባ ሁኖ መልእክት ለማስተላለፍ አልቻለም።

በግል ሳየው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነቱን አስምሮበታል፤ እንኳን ለሃያ አመታት አምባገነን ሁኖ ለገዛ፤ ለተራ ሰው ያለቅሳል፤ ያዝናል። አንዱም መለያችን ይህ ነው። ኢትዮጵያዊነቱን፤ ሰብእነቱን፤ አስመስክሯል። ሁኔታው ቢፈቅድለት ኖሮ፤ አጼ ሃይለስላሴ ሲያርፉ፤ አገር አቀፍና አለም አቀፍ በሆነ መልኩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ባለቀሰ ነበር። የሚያሳፍረው፤ የደርግ መንግስት፤ በጊዜአቸው የሚያኮራ ስራ የሰሩትን፤ በአፍሪካና በአለም ለሃገራችን እውቅና ከፍ ያለ አስተዋጾ ያደረጉትን መሪ፤ በድብቅ እንዲቀበሩ አደረገ፤ ክብራቸውን በመግፈፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብር ገፈፈ። በዚያ ጊዜ የነበሩ እንደሚያስታውሱት፤ በብዙ ሽህ የሚቆጥሩ ኢትዮጵያዊያን በእየቤታቸው አልቅሰዋል። ከዚያ ወዲህ፤ የሃገራችን ሁኔታወች አስደናቂ በሆነ መልክ ተለውጠዋል። ከግማሽ በላይ (**More than 50 percent of the Ethiopian** population of 94 million today) የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው አንድ መሪ ብቻ ነው፤ መለስ ዜናዊን።

ከንግስት ዘውዲቱ በኋላ፤ (መቶ አመት ሊጠጋ ነው)፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጤና ምክንያት ከዚህ አለም ያለፈ መሪ ሲቀብር የመጀመሪያው መለስ ናቸው። ከሃዘኑ ባሻገር ልብ ብለን ማየት ያለብን፤ መለስ የተለቀሰላቸውና የተቀበሩት እንደ አንድ ብሄር ተወካይ ወይንም **እንደ እንደ ትግራይ** ተወላጅ ሳይሆን፤ "እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መሪ፤ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ" ሆነው ነው። ይህን "አዲስ ኢትዮጵያዊነት" ከላይ ሁኖ ያዘዘው የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር ነው። በትእዛዝ የተገኘ "ኢትዮጵያዊነት" ለሃያ አመታት **የተሰሩትን በደሎች እንድንቀበል፤ እንድንረሳ፤** ሊያደርግ አይችልም። ስለዚህ ሁኔታ፤ ቢያንስ በአራት መጽሃፎች ላይ መለስ የመሩት መግንስት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን

በደል በማስረጃ አቅርቤዋለሁ፤ ሁለቱን መጽሃፎቸን እራሳቸው እንዳነበቡና “እንደተቹብኝ” ሰምቻለሁ። ከደጋፊወቻቸው ጋር በይፋ ተከራክሪያለሁ።

በመጻህፍቶች ላይ ለማሳየት የሞከርኩት፤ የአምባገነኑ መንግስት በተራው ሰው ላይና በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን በደል ነው። በተለይ፤ ከግል መብትና ነጻነት፤ ከሰው ህይወት አንጻር ሲታይ፤ መለስ የመሩት መንግስት፤ የገነቡት ስርአት፤ ቀጭ ሁኖ ይገኛል፤ ከፋፋይ ሁኖ ይታያል፤ አገርን የከፋፈለ፤ የተፈጥሮ ሃብትን ለውጭ ግለሰቦችና መንግስታት ያስተላለፈ ሁኖ ይታያል፤ ለውጭ መንግስታት አጎብዳጅ መሆኑን ያሳየበት ማስረጃ ሞልቶ ይታያል። ይህ ጨቋኝ ስርአት መለወጥ አለበት የምለውም በዚህ ምክንያት ነው። ለቅሶው እነዚህን ጉድለቶችና በደሎች አይለውጥም።

**በሞት ወቅት ኢትዮጵያዊ መሆን ምን ትርጉም አለው?**

**እኔንና ሌሎች ተመልካቾችን የሚገርመን፤ ኢትዮጵያዊነታቸው** እውቅና ያገኘው ከዚህ አለም ሲሞቱ መሆኑ፤ ነው። አንዱ የምንማረው ትምህርት፤ መለስ በኢትዪጵያዊነታቸው ከኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ፤ ከኢትዮጵያ ዋና መታወቂያ ቤተክርስቲያን ከተቀበሩ (ማለትም፤ በአዲስ አበባ)፤ በናቁትና፤ “ጨርቅ ነው” ባ<u>**ሉት ሰንደቅ አላማ” ከተሸፈኑ፤ ህወሓት የተባለው በጠባብ ብሄርተኝነት የተመሰረተው የፖለቲካ ራእይም አብሮ ተቀበረ ማለት ነው።**</u> **ጠባብ ዘረኝነት ከተቀበረ እልል ብለን መቀበል አለብን። ሌላም አይነት ዘረኝነት እንዳይደገም ማውገዝ አለብን። አንዳንዶች እንደሚሉት፤** ትግራይ፤ አድዋ ቢቀበሩ ኖሮ፤ የአለምና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፤ ይደንቀውና ይበሳጭ ነበር የሚል ትርጉም ይሰጥ ነበር የሚል ነው። ሌሎች የሚሉት፤ “በጠባብ ብሄርተኛነት” የታወቁት ጠቅላይ ሚንስትር “አድዋ/ትግራይ” እንጅ የኢትዮጵያ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ መቀበራቸው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስድብ ነው የሚል ነው።

የምጋራው፤ ከዱሮውም እንቃወም የነበረው፤ በጠባብብሄርተኝነት፤ ለጠባብ ብሄርተኝነት መደራጀትን ነበር። ለአንድ ብሄር አድልወ ማድረግን ነበር፤ የራስን ብሄር ቡድን ማበልጸግን ነበር። ኢትዮጵያዊነታቸው ከዚህ አለም እስከሚያልፉ ድረስ መቆየቱ፤ ለቀሩት ስልጣን ማጠንከሪያ ከሞሆን ባሻገር ትርጉም የለውም የሚለውን አስተሳሰብ የሚያጠናክረው ለዚህ ነው። ከአሁን በኋላ በብሄር መጠራት፤ በብሄር መደራጀት፤ ለብሄር ማሰብ፤ በብሄር መበልጸግ፤ የማይጠቅመው፤ ትርጉም የማይኖረውም ለዚህ ነው። ቀብሩ እንደዚህ ከላይ የታዘዘ መሆኑ፤ ያከራክራል፤ ያጠያይቃል። በህይወት በነበሩበት ወቅት፤ “እኔ በብሄሬ ሳይሆን፤ የምኮራው በኢትዮጱያዊነቴ ነው ቢሉ ኖሮ” ታሪካዊ ስራ ሰሩ ለማለት እችል ነበር። አላደረጉም። ሆኖም፤ የቀብራቸው ስነስርአት የለውጥ ምልክት ነው ለማለት አንዳንድ ምልክቶች አሉ። ወደፊት የምንፈልጋት ኢትዮጵያ፤ ለሁሉም እድል የምትሰጥ፤ ሁሉም የሚኮራባት፤ ሁሉም በፈቃዱ መሪወቹን የሚመርጥባት፤ አልቅሶ የሚቀብርባት አንድ፤ ፍትሃዊ ሃገር መሆን ይኖርባታል። ከሆነ፤ ሆይ “ብለን እንመርጣለን፤ ወይ ብለን” እንቀብራለን ማለት ነው። ነጻነት ማለት ይህ ነው።

ታዛቢወች ለቅሶውን “በአስከሬን መነገድ፤ ምን ትርጉም አለው” የሚሉት ጠቅላይ ሚንስትር መለስ በህይወት በነበሩበት ወቅት የሰሩት፤ ያለፈውና ያሁኑ “የሕዝብ ትርኢት” ምንም ግንኙነት ስለሌላቸው ነው። ለምሳሌ፤ ከኤርትርያ ጋር ጦር ተካሂዶ፤ ብዙ ሽህ ኢትዮጵያዊን ሞተው፤ ብዙ ቢሊዮን ብር ጠፍቶ፤ አሰብን ለማስመለስ ሲቻል፤ የመለስ መንግስት የሸሸበት ምክንያት ለምንድን ነው? መረጃወች የሚያመለክቱት፤ መለስ፤ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም፤ ታሪክ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ንቀት ነበራቸው፤ ለኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ንቀት ነበራቸው፤ ለተቃዋሚው ንቀት ነበራቸው፤ ለራሳቸው ነገድ አድናቆት ነበራቸው። ሰድበው ለሰዳቢ አስተላልፈውናል፤ ሱዛን ራይስ ስትሰደበን፤ ከመለስ የተማረችውን መነሻ

አድርጋ ነው፤ ፈጥራ አይደለም። በተለይ፤ ለተቃዋሚው ክፍል ያላትን ንቀት ነው ያቀረበችው። ከመለስ ባገኘችው ግንዛቤና ድምደማ መሰረት ነው የሚሉ ብዙ ታዛቢወች አሉ። እኔ የማሳስበው፤ ይህን ሁሉ እንርሳ ሳይሆን፤ ታዝበን፤ ከወቀሳ፤ ወደ ኢትዮጵያዊ ለውጥ ማተኮር አለብን የሚል ነው። አለበለዚያ፤ ሙተውም መለስ እንደተፈለገው ከመቃብራቸው የእኛን አስተሳሰብ ይዳኙታል፤ ይገዙናል። እንደዚህ ከሆነ፤ ሁኔታው  የሚያመልከተው የእኛን ደካማነት ነው።

ያየነው፤ ዱብ እዳ ስለሆነ፤ የሚነሳው ጥያቄና መጠራጠር ተገቢነው። መልሱን፤ ለታሪክ ተመራማሪወች፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እተወዋለሁ። የሕዝቡ በብዛት መውጣት ትርጉም እንዳለው ግን አምናለሁ። ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉት በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ፤ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን አገልጋይ የሆነ መንግስትና መሪ ነው። መጓዝም ያለብን በዚህ በኢትዮጵያዊነት መንገድ፤ ለመላው ኢትዮጵያዊያን አገልጋይ የሆነ ፍትሃዊ ስርአትን ለመገንባት ነው። ይህ ቀላል መንገድ አይደለም። የህወሓት/ኢህአዴግ ብዙ ዘርፍ ያለው አገዛዝ መለስ በማለፋቸው አልተለወጠም። ቅድመ ሁኔታወች ተስተካክለው፤ ሁሉን የሚያካትት መንገድ ካልተቀየሰ፤ የአምባገነኑ ስርአት እንዳለ ይቆያል፤ አደጋው በዚያው ልክ ያይላል። አደጋው፤ ለሌቻች ብቻ ሳይሆን፤ ለህወሓት/ኢህአዴግም ጭምር ነው። ሰላምን የነሳ በሰላም ለመኖር አይችልም የምለውም ለዚህ ነው።

ለዚህ ነው፤ የጠቅላይ ሚንስትሩ አድናቂወች፤ ለኢትዮጵያ እርጋታ፤ ለመላው ሕዝቧ ሰላም፤ ከርሃብ አለንጋ፤ ከስደት፤ ከበሽታ፤ ከጠለላ ማጣት ወዘተ ነጻ መሆን ካሰቡ፤ የስርአቱን ደካማ ጎን ጭምር ማሳየት ይኖርባቸው የነበረው። ለማሳየትም የዲፕሎማቲክ ፕሮቶኮል ካልፈቀደ፣ አድናቆቱን ለዛ፤ ሚዛናዊና እውነተኛነት በተሞላበት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ አላዋቂ በማያደርግበት መልክ ማቅረብ የነበረባቸው። ህዝቡ ብሶቱን ያውቃል። እድገት ያለ ፍትሃዊ ልማት ትርጉም እንደሌለው ያውቃል። ሌሎች ፍትሃዊ የሆኑ የአፍሪካ አገሮችን ማየት ብቻ ይበቃል።

አበዳሪወች/ደጓሚወች፤ የሚያውቁት የማይናገሩት፤ ከሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ሌላ፤ ኢትዮጵያ፤ እአአ በ2011 በጤና ጥበቃ ግልጋሎት ከአለም 109 ኛ፤ በንጹህ ውሃ አቅርቦት፤ ከአለም የመጨረሻ፤ በሰው ኑሮ ደህንነት (**Human Safety and Security**) ከአለም 106 ኛ ፤በሰብአዊና ግለሰብ ነጻነት፤110ኛ **(<u>ከሁሉም አገሮች ነጻነት የሌለባት)</u>፤** በዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጅ አቅርቦት፤ እንደ ኢንተርኔት ያሉ፤ ከመቶ አገሮች ሃያ አምስተኛ፤ በመኖሪያ ቤት የማግኘት እድል፤ ከ108 አገሮች ዘጠና-አንደኛ፤ በህግ የበላይነት 101ኛ ፤ በግለሰቦች መካከል ባለው የገቢ/የኑሮ ልዩነት (**Income, wealth and social (jobs, education, health inequality**) 20ኛ፤ናት። እነዚህን ልዩነቶች የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በቀላሉ ልያጠፋ ይችላል ማለት ዘበት ነው። ሰላም፤ እርቅ፤ ህብረት፤ ፍትህ የሚያስፍልገው ለዚህም ጭምር ነው። በሰብአዊና ግለሰብ መብቶች በኩል ያለው ጫና ከሁሉም በላይ አሳሳቢ መሆኑን፤ የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር (**Department of State**) በእየአመቱ የሚያወጣው ዘገባ ብቻ ይበቃል።

ፊዝ ካሪሚ በሲኤንኤን September 3, 2012, "የስብአዊ መብት ተቋሞች እንደሚሉት ከሆነ፤ መለስ የግለሰቦችን ነጻነትና መብቶች ደጋግመው ጥሰዋል፤ የመገናኛ ብዙሃንን አጥፍተዋል፤ ጋዜጠኞችን አስረዋል፤ አሳደዋል፤ ተቃዋሚ ድርጅቶችንና መሪወችን መንጥረዋል....የምእራብ አገሮች ይህ ሁሉ ሲሆን፤ የመለስን ድክመት እንዳላዩ አልፈውታል። ለነሱ፤ መለስ ጸረ-ሽብርተኛ ሁኖ በአፍሪካ ቀንድ መቆም የወዳጅነት ዋና መለኪያ ሁኗል።" ጠናካራ ጎን ብቻ በማንሳት፤ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት ተቃዋሚ የሆነውን ሁሉ መግደልን፤ ማሰርን፤ ማሳደድን፤ ከሃብት ከመሬት ማስውጣትን የአገዛዙ ስልት አድርጎ መጠቀሙን ችላ አሉት ማለት ነው። ይህ፤ አያዋጣም፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ፤ ፍትሃዊ ስርአት ግን፤

ለሰላም፤ አብሮ ለመኖር፤ የሃገራችን ግዛታዊ አንድነት ለመጠበቅ፤ ድሃውን ከድህነት ነጻ ለማውጣት፤ ጠንካራ ህብረተሰብ ገንብቶ ሽብርተኞችን ለመከላከል ያስችላል። ይህም የጊዜው ዋና ጥሪ ነው።

የአጃንስ ፍራንስ ፐሬስ ጀኒ ቮጋን፤ በ September 1, 2012, ሚኬላ ሮንግን (Michela Wrong, an authority on ethnic elites in Africa) በመጥቀስ፤ የመለስን ማረፍ እንዲህ ብለው አስቀመጡት። "የገዢ መደብ የበላዮች (**the Ruling Elites**) ፍላጎት ጥቅማቸውን ማስከበር ብቻ ነው። እርጋታን የሚፈልጉት ለዚህ ነው።" እርጋታ መፈለጋቸው በቀጥታ ከምእራባዊያን መንግስታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናክርላቸዋል። ሁለቱም፤ ከነጻነትና ከእውነተኛ ዲሞክራሳዊ ስርአት በላይ እርጋታን ይፈልጋሉ። ተቃዋሚወችም ሆኑ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ይህን የተሳሰረ የጥቅም ግንኙነት በመነጋገር ለመፍታት ካልቻሉ፤ የትም ልንደርስ አንችልም። ሁለቱም ወገኖች፤ የተፈጠረውን የእድል ቀዳዳ ተጠቅመው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሩህ የሆነ አቅጣጫና መልስ መስጠት አለባቸው ማለት ነው። ሁለቱም ወገኖች፤ በመጀመሪያ ማመን ያለባቸው፤ መልሱን ለመስጠት የሚችለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ለመብቱ ሲቆም፤ ድምጹን ያለገደብ ሲሰጥና ሲታገል ብቻ መሆኑን ነው።

<u>**የገዥው ፓርቲ ሆነ፤ የተቃዋሚወች አገልጋይነታቸውና ተጠሪነታቸው ለድርጅት/ለግለሰብ ስልጣን ወይንም ለአንድ**</u> ብሄር/ብሄረሰብ፤ ለአንድ ግለሰብ ዝና፤ ሳይሆን፤ ለኢትዮጵያና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ካወቁ ሌሎች ችግሮች በሂደት ይፈታሉ። ፈቃደኛነትና አርቆ አስተዋይነት ካለ፤ የማይፈታ ነገር የለም።በሌላ አነጋገር፤ የትግሉ አላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሳዊ ስልጣንና የበላይነት፤ የትግሉ ሜዳ፤ ኢትዮጵያ፤ ታጋዩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው በማለት በመደጋገም ከሌሎች አገሮች ልምድና ከኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋእትነት ጋር በማያያዝ ያቀርብኩትን ዘገባ አስታውሳለሁ። ይህን ስል፤ ከውጭ ያለው ታጋይ ሚና የለውም ማለቴ አይደለም፤ በውጭና በውስጡ የጠበቀ ግንኙነት (Organic link) እንዲኖረው መጣር አለብን ማለቴ ነው።

ከአንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች እንደሚነገረው ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን የመንግስት አይነት ያውቃል። ታሪክ አለው፤ የትግል ታሪክ ጭምር። የጎተትነው እኛው ራሳችን ነን። ጫና ያደረገበት የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን አመራር ያውቃል። ለስልጣን ያለውን ሩጫ ጠንቅቆ ያውቃል። ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ ያውቃል። በአቋራጭ፤ አገሪቱንና መላው ሕዝቧን ሳያስቀድሙ፤ ለስልጣን የሚሮጡትን ለይቶ ያውቃል። ለአደጋ የሚዳርጉትን ያውቃል። ሕዝቡ፤ የህወሓት/ኢህአዴግ ስርአት፤ አገዛዙ የተዛባ፤ ጸረ- ፍትህ መሆኑን ካወቀ አመታት ሁኖታል። ይነሳል የምለው ለዚህ ነው። አስተማሪ አያስፈልገውም፤ አጋር እንጅ። አሁንም የህዝቡን ለውጥ ፈላጊነት በየቦታው በእውን እያየነው ነው። ህዝብ ያልፈለገው፤ ያልመረጠው፤ መንግስትና አመራር ያስከተለውን ጉዳትና በደል ጠንቅቆ ያውቃል። ለለቅሶ መውጣቱ ያለውን ብሶትና ሰቆቃ እንደማይሸፍነው የተረዳ ሕዝብ ነው ለማለት የሚያስችሉ መረጃወች እንደገና እነሆ፤

i) በሃይማኖት ነጻነት ላይ የሚደረገው ጣልቃ ገብነት ለሃገራችን አደገኛ መሆኑ፤ አብሮና ተቻችሎ ለሚኖረው ህብረተሰብ እርጋትና ሰላም መንሳቱ፤

ii) የጠባብ ብሄርተኛ የፖለቲካ አቀራረጽ ለግለሰብ መብቶች፤ ለህዝብ ነጻነት፤ በእኩልነት ብቻ ለሚገኝ ህብረት ማነቆ መሆኑ፤ ለሃገር ግዛታዊ አንድነት ጸር መሆኑ፤ ለጥቂት የበላዮች (Ethnic elites) የፖሌቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት አስተማማኝ መሆኑ፤

iii) አድሏዊ የሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአት ለወጣቱ ትውልድ እድል ፈጣሪ ሳይሆን፤ ለስደት የዳረገው መሆኑ፤ ስደት ለክብርና ለዜግነት/ለኢትዮጵያዊነት ማነቆ መሆኑ፤

iv) ጥቂት የህወሓት/ኢህአዴግ ቤተሰቦች፤ ግለሰቦች፤ የፓርቲው ተቋሞች ኢኮኖሚውን በሙሉ ቁጥጥር ስለያዙት፤ ነጻ የገበያ ውድድር መጥፋቱ፤ ኢኮኖሚው የፍጆት እቃወችን፤ ምግብን፤ ወዘተ ለማቀርብ አለመቻሉ፤ አቅርቦትና ፍላጎት የሰማይና የምድር ያህል መራራቃቸው፤ የዋጋ ግሽፈት ተራውን ሆነ መካከለኛውን መደብ ማደህየቱ፤ ህዝቡ ቤት ለመግዛት ቀርቶ ለመከራየት አለመቻሉ፤ ልጆችን ማስተማር ህልም እየሆነ መሄዱ፤

v) ህወሓት/ኢህአዴግ የትምህርት እድል አስፋፋ ቢባልም፤ ትምህርቱ ጥራት የሌለው መሆኑ፤ የተማረው ወጣት እጣው ስደት መሆኑ፤ ስደተኞች በሚሄዱበት ሁሉ ክብራቸው መገፈፉ፤ ህይወታቸው ለአደጋ መዳረጉ፤

vi) ሌሎች አገሮች የመገናኛ ብዙሃን መስፋፋት፤ የዘመናዊ የመገናኛ ቴክኖሎጅ መለቀቅ ለነጻነትና ለእድገት ከስራ ላይ ሲያውሉ፤ ገዥው ፓርቲ ቁጥጥሩን አስፋፍቶ፤ ቴክኖሎጅን ለስላ ማዋሉ፤ እድልን መወሰኑ፤ ተማሪወች፤ አስተማሪወች የመፍጠር፤ የማሰብ፤ የመጻፍ መብታቸው ታግዶ ፓርቲው ያለውን ብቻ ተቀበሉ መባላቸው፤ በገፍ አባል እንዲሆኑ መገደዳቸው ለአገሪቱ እድገት ማነቆ መሆኑ፤ በውጭ የሚገኙ እውቀትና ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ለሃገራቸው አስተዋጾ ለማድረግ ሲችሉ፤ አስቃቂ ክትትል፤ ገደብ መደረጉ፤

vii) ነጋዴ ሆነ ታክሲ ነጅ፤ አስተማሪ ሆነ፤ ተማሪ፤ የመንግስት ሰራተኛ ሆነ የግል ንብረት አንቀሳቃሽ፤ የሚጠይቀው ተገቢ ጥያቄ አለመመለሱ፤ እንዲያውም፤ ጠያቂወች እንደወንጀለኛ እየተቆጠሩ ችግር ላይ መውደቃቸው፤ ገንዘብ ለማሸሽ ዋና ምክንያቱ ስርአቱ መሆኑ፤ ለህዝብ ኑሮ ተፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋቸው አስተማማኝ በሆነ መንገድ ሊቀርቡ አለመቻላቸው፤

viii) የቀረው አለም፤ በተለይ እንደ ጋና፤ ቦትስዋና፤ ኬንያ፤ ናይጀሪያ ያሉ የአፍሪካ አገሮች የፕሬስ ነጻነትን ጥቅም አይተው ስራ ላይ ሲያውሉ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ጋዜጠኞችን ማሰሩ፤ ከሃገር ማባረሩ፤ የመናገር፤ የመጻፍ፤ የመሰብሰብ፤ የመደራጀት መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማገዱ፤ ይህም ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ ጸር መሆኑ፤

ix) ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት፤ የተደራጁ፤ በሰላም ብቻ የሚሰሩ፤ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በተከታታይ ህልውናቸው እንዲጠፋ መደረጉ፤ መሪወቻቸውና አባሎቻቸው በግልጽና በድብቅ መገደላቸው፤ በይፋ ባልሰሩት ወንጀል መታሰራቸው፤መሰደዳቸው፤ የመድብለ ፓርቲ ሚና ፍጹም በሆነ ደረጃ መጥፋቱ፤

x) በምርጫ ዘጠና ሰባትና በ 2002 ኢ.ም. ህወሓት/ኢህአዴግ ፍጹምነቱን በማሳየት፤ አፍሪካ ውስጥ ታይቶ በማያውቅ ደረጃ 99.6 % ድምጽ አግኝቻለሁ ብሎ የአለምን ሕዝብ ማጭበርበሩ፤ አምባገነንነትን ፍጹም ማድረጉ፤

xi) በምርጫ ዘጠና ሰባት መሸነፉ ብቻ ሳይሆን፤ ሰላማዊ ወጣቶችን፤ አባቶችን፤ እናቶችን መግደሉ፤ ከአርባ ሽህ በላይ የሚሆኑ ወገኖቻችን ማሰሩ፤

xii) በተከታታይ ለማሸነፍ ሲል፤ የመንግስት ሰራተኞች፤ ተማሪወች፤ ገበሬወች፤ ሴቶች የፓርቲ አባል እንዲሆኑ፤ ከመንግስት ባጀት እየመደበ አባላቱን ወደ አምስት ሚሊዬን እንዲደርስ ማድረጉ፤ በብዙ መቶ ሽህ የሚቆጠሩ ያለፈቃዳቸው አባል እንዲሆኑ ማስገደዱ፤

xiii) ንጹህ ኢትዮጵያዊያንን ለመወንጀል እንዲያመች "የጸረ ሽብርተኛ" ህግ ደንግጎ፤ አገሪቱን ወደ "እስር ቤት" መለወጡ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከራከርለት ነጻ የሆነ የማህበራዊ ድርጅት እንዳይኖር፤

የመንግስት ያልሆኑ ተቋሞችን የሚዳኝ፤ ገደባን የሚያጠናክር ህግ አውጥቶ ከስራ ላይ ማዋሉ፤ የነጻ ፕሬስ እንዳይኖር፤ ህገ መንግስቱን በመጣስ፤ የፕሬስ ነጻነት ሙሉ በሙሉ እንዲታገብ ማድረጉ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ ማጎሩ፤

xiv) በጋምቤላ፤ አኝዋኮችን በገፍ እየገደለ አልገደለኩም ማለቱ፤ በኦጋዴን ሴቶች፤ ልጆች፤ እናቶች፤ አባቶች እያሳደደ፤ እየገደለ፤ ሴቶችን እያስደፈረ፤ ለዚህም ተጠያቂ አይደለሁም ማለቱ፤ በአማርኛ ተናጋሪወች ላይ፣ በተደጋጋሚ፤ ከቀያቸው እንዲሰደዱ፤ ከመሬታቸው እንዲወገዱ ማድረጉ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ፤ በተለያዩ ቦታወችና ወቅቶች እንዲገደሉ፤ በገደል እንዲወረወሩ፤ የዘረኛ ቂም በቀል በንጹህ ኢትዮጵያዊያን ላይ እንዲካሄድ በተከታታይ እያወቀ እንዳላወቀ ማየቱ፤ ማካሄዱ፤

xv) ምርጥ የትግራይ ግለሰቦች፤ የህወሓት የበላይ ቤተሰቦች፤ ታማኝ የኢህአዴግ መሪወች፤ ከውጭ አገር አጋሮች ጋር ሁነው የአገሪቱን ቁልፍ የኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲቆጣጠሩ ማድረጉ፤ ከአራት ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሚሆን ለም መሬትና ወንዝ ለውጭ አገር መንግስታት፤ ለግለሰብ ኢንቤስተሮች፤ ለምርጥ የትግራይ ተወላጆች ያለ ገደብ፤ ያለ ግልጽነት፤ ማስተላለፉ፤ ነዋሪወችን ከቀያቸው ማስወጣቱ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩትን ለስደት መዳረጉ፤

xvi) ከሰሜን ሱዳን መንግስት ጋር በመመሳጠር፤ ከአንድ ሽህ ስድስት መቶ ስኩየር ኪሎሜትር በላይ የሚገመት የኢትዮጵያ አንጡራ የተፈጥሮ ሃብትና መሬት ለሱዳን መንግስት በድብቅ፤ መስጠቱ፤

xvii) ኤርትራን ከእናት አገሯ ለይቶ ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽና ፍላጎት እንድትገነጠል ማድረጉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዙ ቢልዬን ብር ያሰራቸውን ወደቦች፤ በተለይ ለውጭ ንግድ ቁልፍ ወደብ የሆነችውን አሰብን ሆነ ብሎ ለኤርትርያው ኢሳይያስ አፈወርቂ መንግስት ማስረከቡ፤ ስለሆነም፤ ኢትዮጵያን በታርኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደብ አልባ ማድረጉ፤ እድገቷን፤ ጸጥታዋን፤ ደህንነቷን ለአደጋ መዳረጉ፤

xviii) የኢኮኖሚውን ፖሊሲ (አመራር)ና መዋቅር ለመለወጥ ባለመቻሉ፤ ኢትዮጵያ ከመቸውም የበለጠ የለጋሽ አገሮች፤ ጥገኛ እንድትሆን ማድረጉ፤ ይገኙበታል።

እነዚህ ሁሉ በደሎች፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ጉዳት አላቸው። መለስ በበላይነት የመሩት የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት እነዚህን ሁሉ መዋቅራዊና ስርአታዊ ማነቆወች (**Structual and Systemic Hurdles**) ለተተኪው ትውልድ አውርሷል። ያለ መላው ሕዝብ ተሳትፎ፤ ቢፈልግም እንኳ፤ የብቸኛ አመራር መከተሉን ከቀጠለበት፤ ስርአታዊ ችግሮችን ሊፈታቸው ቀርቶ፤ ሊያሻሺላቸው አይችልም። ልንተነብየው የምንችለው፤ የብቸኝነት አመራሩን ከቀጠለ፤ ሊያባብሳቸው እንደሚችል አመልካቾች አሉ። ለማጠቃለል፤ የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር ካወቀበት፤ መፍትሄው በፊታችን ይታያል። በመጀመሪያ፤ የፖለቲካ ምድሩን ለተቃዋሚወች ሁሉ ክፍት ማድረግ አለበት የምለው ለዚሁ ነው።

**ይህን ክፍል ለማጠቃለል፤**

***ፈተናው አምባገነናዊ ስርአት ለማንም አያዋጣም ብሎ መቁረጥና መፍትሄወችን በጋራ ተወያይቶ ከስራ ላይ ከማዋሉ ላይ ነው። አገራዊ፤ ሁሉን አቀፍ፤ የሰላም፤ የእርቅ፤ የፍትህ፤ የዲሞክራሲ ግንባታ፤ ሁሉን አቀፍ አገራዊ ስብሰባና የሽግግር ውይይት በአስቸኳይ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ለዚህ የተቀደሰ፤ ታሪካዊ ጥሪ፤ ህወሓት/ኢሃዴግ፤ አዲሱ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚንስትር፤ ተቃዋሚወች በሙሉ፤ ለኢትዮጲያ ሕዝብ የሚያስቡ የአለም ህብረተሰብ አባላት ሁሉ፤ በፍጥነት ውይይት፤ ንግግር ማድረግ***

አለባቸው። ቅድመ ሁኔታወችን ማመቻቸት አለባቸው። ከሁሉ በላይ፤ ሑሉን አቀፍ የሆነ አገራዊ ስብሰባ፤ ውይይትና ድርድር የሚጠቅመው ኢትዮጵያንና መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ በተለይ፤ ተከታታይ ትውልድን ለማገልገል ነው በማለት እደመድማለሁ። እያንዳንዳችን ያለብን ሃላፊነት፤ አገር ቤትና ውጭ ያሉ ተቃዋሚወች ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደ ጎን አድርገው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት የሚሆንበትን መንገድ (Road Map) ከስራ ላይ ማዋል ነው። ለአዲሱ አመት የምመኘው ይህንኑ መሆኑን ለአንባቢው እገልጻለሁ።

ይቀጥላል

9/10/2012